የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፩
አዲስ አበባ— ግንቦት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 41
ADDIS ABABA - 4th June, 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፭/፲፱፻፺ ዓ·ም·
ለማዳበሪያ ግዥ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ በከፊል ለመሸፈን ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት
ማጽደቂያ አዋጅ ...................................... ገጽ ፯፻፶

## CONTENTS

Proclamation No. 115/1998
African Development Fund Loan Agreement for Financing Part of the Foreign Exchange Cost of the National Fertilizer Sector Project Ratification
Proclamation ...................................................... Page 750

## አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፭/፲፱፻፺

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለማዳበሪያ ግዥ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ በከፊል ለመሸፈን የሚውል መጠኑ ዩ·ኤ· ፳፰ ሚሊዮን (ሃያ ስምንት ሚሊዮን ዩኒትስ አፍ አካውንት) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ· ፌብሩዋሪ ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ በአቢጃን የተፈረመ በመሆኑ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈጻሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስላለባቸው፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም· ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ፤

በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለማዳበሪያ ግዥ ማስፈጸሚያ የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ በከፊል ለመሸፈን ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፭/፲፱፻፺" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 115/1998
### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund, stipulating that the African Development Fund provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of UA 28,000,000 (twenty eight million Units of Account) for financing part of the foreign exchange cost of the National Fertilizer Sector Project, was signed in Abidjan, on the 20th day of February, 1998;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to entry into force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 4th day of June, 1998;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for Financing Part of the Foreign Exchange Cost of the National Fertilizer Sector Project Ratification Proclamation No. 115/1998."

ያንዱ ዋጋ 2·30
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ·ኤ·አ· ፌብሩዋሪ ፳ ቀን ፲፱፻፺፰ በአቢጃን የተፈ ረመው ቁጥር ኤፍ/ኢቲኤች/ኤንኤቲ–ኤፍኢአር/፺፰/፴፰ የብድር ስምምነት ነው።

፫· የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ዩ·ኤ· ፳፰ ሚሊዮን (ሃያ ስምንት ሚሊዮን ዩኒትስ አፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. F/ETH/NAT-FER/98/38 signed in Abidjan, on the 20th day of February, 1998 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of UA 28,000,000 (twenty eight million Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 4th day of June, 1998.

Done at Addis Ababa, this 4th day of June, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE